

# የአቶ ገብረ ጻድቅ ሃደራ አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ ገብረጻድቅ ሃደራ ከአባቱ ከአቶ ሃደራ ባርዮሐንስ ከእናቱ ከወይዘሮ ምጽላል ገብረ በትግራይ ክልል በክለተ አውላሎ አውራጃ ፍረወይኒ (ስንቃጣ) ከተማ ተወለደ። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ በአጼ ዮሐንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት ካጠናቀቀ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርቱን መቀሌ አጼ ዮሐንስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኮሜርሺያል አካውንቲንግ በተለየ ከፍተኛ ማእረግ ተመረቀ። ገብረጻድቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረበት ሰዓት በክፍለ ሃገሩ የታወቀ የአጭርና እረጅም እሯጭ በመሆን ክፍለ ሀገሩን ያስጠራ ታዋቂ እስፖርተኛም ነበር። ለተከታታይ ትምህርት በነበረው ጽኑ ፍላጎት ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ በመግባት በዲፕሎማ ተመርቋል። አቶ ገብረጻድቅ ሃደራ በኮተቤ በነበረበት ሰዓት አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በመመዝገብ የዩንቨርሲቲ ኮርሶችንም ይከታተል ነበር።

- በ ሐረር ክፍለ ሐገር በቀላፎ በመምህርነት
- በዳሬክተርነት
- በቱሉ ቦሎ በዳሬክተርነት
- በትግራይ ክፍለ ሃገር በሃገረ ሰላም ትምህርት ቤት በዳሬክተርነት ሲያገለግል ቆይቶ እንደ ገና ወደ ተማሪነት በመመለስ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በመግባት በትምህርት ላይ እንዳለ የወቅቱ አብዮት ፈናዳ። ደርግ የእድገት በሕብረት ዘመቻን ካወጀ በኋላ ሃደራም በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ወረዳ በአዝማችነት ተመድቦ አገልግሏል።

የተቀጣጠለው ዓብዮት እየተፋፋመ በሄደበት ወቅት አቶ ገብረ ጻድቅ ሃደራ ከመሰል ተራማጅ መምህራንና ተማሪዎች ጋር በመሆን በተለያዩ የጥናት ሕዋሳት ውስጥ በመግባት መደራጀትና ማደራጀትን ጀመረ። ሃደራ በነበረው ቆራጥ የትግል ፍላጎት ባሳየው ከፍተኛ የአመራር ብቃት በወቅቱ በነበረው የኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ ሰክረተሪየት ተብሎ በተዋቀረው በማእከላዊ ኮሚቴና በዞን መካከል ባለ ኮሚቴ ውስጥ ከማገልገሉም በላይ ድርጅቱ የተለያዩ የድርጅት ሥራዎችን እንዲሰራ በሰጠው የሥራ ድርሻ ሁሉ ሃላፊነቱን ከሚገባው በላይ የተወጣ ግለሰብ ነው። ለብዙ የድርጅት ግለሰቦችና ክፍሎች የፓርቲዉ አገናኝ ሆኖ ከማገልገሉም በላይ የተጋለጡ ታጋዮችን መደበቂያ አዘጋጅቶ በመደበቅ ወደ ሜዳ መላክ የነበረባቸውን ታጋዮች መታወቂያ በማሰራት የማምለጫ መንገዶችን በማዘጋጀት በሰላም ወደ ትግል ሜዳ እንዲገቡ በሃላፊነት የሚያስፈጽመውና የሚፈጽም ታጋይም ነበር። አቶ ገብረ ጻድቅ ሃደራ በዚያን የደርግ የቀውጢ ሰዓት በሕይወት ከተረፉት ጥቂት የበላይ አመራር አባላት ጋር በመሆን ቤተሰቡን በትኖ ሕይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ ከብዙ ችግርና ፈተና ያመለጠ ቆራጥ ታጋይ እንደነበረ የሚመሰክሩ ብዙዎች ናቸው። ሃደራ የከተማውን ግዳጅ ፈጽሞ የኢሕአፓን ሰራዊትን ተቀላቅሎ በአሲምባ በጎንደር ሲንቀሳቀስ ቆይቶ በመጨረሻ ብዙሃኑ ታጋይ ወደ ስደት ሲዳረግ፣ እሱም ወደ ሱዳን ለመሰደድ ተገደደ።

ሃደራ በ1980 ዓ ም ወደ አሜሪካን ሃገር በስደተኝነት መጥቶ እንደማንኛውም ስደተኛ የግል ኑሮውን ባዲስ መልክ ጀመረ። ያም ሆኖ ሃገር ቤት ያገባትን ውድ ባለቤቱን ወይዘሮ አመለወርቅ ነጋሽን ትቷቸው የተሰደደውን ልጆቹን ከማሰብና ከመርዳት አላቋረጠም ነበር። ቤተሰቡን መርዳትና እዚህ አሜሪካን ሃገር መጥተው እንዲቀላቀሉት የሚቻለውን ከማድረጉም በላይ እየሰራ ለመማር በወስነው መሰረት፡

1986 ዓ ም ከ UNIVERSITY OF NORTH TEXAS በ ፖለቲካል ሳይንስ የባችለር ዲግሪ።
1988 ዓ ም እንዲሁ ከUNIVERSITY OF NORTH TEXAS በ ፋይናንስ የማስተር ዲግሪ ለማግኘት በቅቷል።

ሃደራ ያልመው የነበረው ሕልም እውነት ሆኖ 1998 ዓ ም ከሚወዳት ከባለቤቱ ጋር በአሜሪካ ተቀላቀለ። ሃደራ የስድስት ልጆች አባት 14 ልጆች አያት ለመሆን የታደለ ግለሰብ ነበር። ሃደራ በሕይወት ያሉ አንድ ወንድምና ሶስት እህቶች ሲኖሩት በአደራ ወንድምነት የሚኮሩ ብዙ እሕቶችና ወንድሞች እንዳፈራ መናገር ግን ማጋነን አይደለም።

ሃደራ በትምህርት ቤት እያለ በትራንስፖርት በፖስታ ቤት የሰራ ከመሆኑም በላይ ከተመረቀ በኋላ በ BUSINESS CONTROL SYSTEM መስሪያ ቤት CHIEF CONTROLLER በመሆን ስርቷል። ለተወሰነ ጊዜ የግል ንግድ በማቋቋምም፣ ሲሰራ ቆይቷል። እስከ መጨረሳው ሰዓት ደግሞ በትራንስፖርት ሥራ ላይ ተሰማርቶ ይገኝ ነበር። አቶ ገብረጻድቅ ሃደራ MR. BERNIY FRANCIS ለካርልተን ሲቲ ካውንስልነት በሚወዳዳደርበት ሰዓት የካምፔን ማናገጀር በመሆን እንዲያሸንፍ ማድረጉን ሲናገር በደስታ ነበር። ሃደራ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ በፈቃደኝነት ያገለገል ሲሆን ጥቂቶችን ለመግለጽ

- የትግራይ መረዳጃ ማሃበር በመሥራችነት
- ዳላስ የውይይት ፎረም
- የአሲምባ ክለብ መሥራችና አባል።
- አጼ ዮሐንስ አሉምኒ (AYAA) በ ምክትል ፕሬዚዳንትነት ብሎም በፕሬዚደንትነት
- ዳላስ ዋልያ ኢንቨስትመንት ክለብ በመሥራችነት።

በአጼ ዮሐንስ አሉምኒ መዋጮና እቅድ እየተሰራ ያለውን ላይበራሪ እያነሳ ከምንም በላይ የተደሰተበት እንደሆነ ሲናገር ሰሚ ይሰልች እንደሆን እንጂ እሱን ግን አይሰለቸውም ነበር።

አቶ ገብረጻድቅ ሐደራ JANUARY 6 ቀን 2013 የሚወዳቸውንና የሚንከባከባቸውን ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን የሚያፈቅራትንና የሚያከብራትን ባለቤቱን ጓደኞቹን ትቶ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ሃደራ ለትንሽ ትልቁ መካሪ ታጋይ ብልህ ለሕጻናት ልዩ ፍቅር ያለው፡ ካመነበት የማያወላውል ቆራጥ ወንድም ነበር።



# እኔ ሳውቀው

ከቀድሞ የኢሕአፓ ፖሊት ቢሮ አባላት አንዱ።

ገ/ጻድቅን ሓደራ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በ1968 ዓም ይመስለኛል። ተስፋዬ ደበሣይ በሥራ ጉዳይ ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ ስለነበረ እሱን ተክቼ አንዳንድ ሥራዎችን ማከናወን ነበረብኝና ለአጭር ጊዜ፣ ተስፋዬ እስከሚመለስ ጊዜ ድረስ፣ አብረን ሰራን። ለሁለተኛና ዘለግ ላለ ጊዜ ከሓደራ ጋር የሰራሁት የኢህአፓ የማእከላዊ ኮሚቴ ተበታትኖ፣ ገሚሱ በትግሉ መስዋእትነት ከፍለው ከወደቁ በኋላ፣ ሌሎቹ ደግሞ ወደ አሢምባ ወደ ውጭና ወደ መሳሰለው በሄዱበት ጊዜ ነበር።

ሓደራ በተለያዩ ቦታዎች በድርጅቱ ተመድቦ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በ1967 ዓም በተደረገው የኢህአፓ መለስተኛ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት ሴክረታርያት ተቋቁሞ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ድርጅታዊ መዋቅሮች በሶስት ቀጠናዎች ስር እንዲዋቀሩ ተደርጎ ስለነበር፣ በአንደኛው የሴክረታርያት አካል፣ ማለትም፣ ኤርትራ፣ ትግራይ፣ ጎጃምና ጎንደርን የሚመለከተውን፣ ከተሥፋዬ ጋር በመሆን አብረው እንዲሰሩ ተመደበ።

- ሓደራ ከሴክረታርያት አባልነቱ ባሻገር፣ በትግራይ ይገኝ የነበረውን የሠራዊት አካል ከማእከላዊ ኮሚቴው ጋር ከሚያገናኙት መሀል ከመሆኑም ሌላ፣በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ወጣቶች የኢህአፓን ሠራዊት እንዲቀላቀሉ ከዝግጅት እስከ ሽኝት ያለውን ሥራ ያከናውኑ ከነበሩ መሀል አንዱ ነበር።
- በአንድ ወቅትም የኢህአፓ የልኡክ አባል በመሆን ከጀብሃ (የኤርትራ ነፃ አውጭ ድርጅት) ጋር ድርድር ለማድረግ ከተላኩት መሀል አንዱ ነበር
- የትግራዩ መስመር እንደተዘጋ፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ አባላትን በከተማዎች ይካሄድ ከነበረው ከፍተኛ እልቂት ለማዳን ከሶስት ጊዜ በላይ ወደ ጎንደር በመመላለስ ‘መስመሮችን’ ለመዘርጋትና ለማስተካከል ጥረት ካደረጉት መሀል አንዱ ነበር። በሓደራና በሌሎች አባላት ጥረትም የተወሰነ ህይወት ሊተርፍ ችሏል።

- የማእከላዊ ኮሚቴው ከተበታተነ በኋላ፣ ከአመራሩ አባላት አዲስ አበባ የቀሩት ሁለት ብቻ ሲሆኑ፣ እነሱም አንድ ውሳኔ ላይ ደረሱ። ውሳኔውም ከሁለቱ የማእከላዊ ኮሚቴ ጋር ሶስቱ የንኡስ ሴክረታርያት አባላት፣ ሓደራንም ጭምር፣ አንድ የጋራ ኮሚቴ እንዲፈጥሩ ስለነበር፣ ሓደራም የዚህ ኮሚቴ አባል በመሆን ድርጅታዊም ሆነ ሀገራዊ ግዳጁን ተወጥቷል።
- ሠራዊቱ ወደ ጠገዴ እንዲገባ ሲወሰን፣ አካባቢውን ለማጥናት ከተላኩት መሀል አንዱ ሓደራ ነበር፣
- የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የአመራር አባላት ለስብሰባ ወደ ሠራዊቱ ሲሄዱ፣ የድርጅቱን ከፍተኛ የአመራር ሃላፊነት ይዘው ከቀጠሉት ጥቂት አባላት መሀል አንዱ ሓደራ ነበር።
- ሓደራ ራሱን ብቻ ሳይሆን ለመስዋእትነት ያቀርብ የነበረው፣ ቤተሰቡንም ጭምር አንደ ነበር መናገር ማጋነን አይሆንም። ቤተሰቦቹ ለስብዓዊ መብት የበኩላቸውን አስተዋጽዎ አበርክተዋል። የሓደራ ቤት መጠለያ አጥተው ይንከራተቱ ለነበሩ መሸሸጊያ ነበር፣
- ሓደራ ልጆቹንና ባላቤቱን የሚያፈቅር፣የሚያከብር ቢሆንም ሀገራዊ ጉዳይን ያለመታከት ሲያከናውን የቆየ አርቆ አሳቢ ሰው ነበር።
- ሓደራ የቀይ ሽብር በጋመበትና በፋመበት በዚያ ዘመን፣ ለራሱ ሳይጨነቅና ሳይጠበብ የተጣለበትን ሃላፊነት ከተወጡ ጥቂት አባላት መሀል አንዱ ነበር።
- በዚያ በክፉ ቀን፣ የሰው ልጅ በተለይም የኢትዮጵያ ወጣቶች እንደ አውሬ እየታደኑ ይገደሉ፣ ይረሸኑ፣ ደማቸው በየአደባባዩ ይፈስ በነበረበት ጊዜ፣ ሓደራ ይህን አሰቃቂ ስርዓት በቁርጠኝነት ከታገሉ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች መሀል አንዱ ነው። ሓደራ እዚያው እሳቱ ውስጥ ተማግዶ ታግሏል፣ አታግሏልም። ሓደራ፣ እንደ ጅረት ይፈስ የነበረውን የወጣቶች ደም ለመታደግ፣ የእናቶች እንባን ለማበስ ቤተሴቤ፣ ልጆቼ፣ ባለቤቴ ሳይል ህይወቱን ጭምር አሳልፎ የሰጠ ጀግናና ክቡር የኢትዮጵያ ልጅ ነበር።
- ከተስፋዬ ደበሣይ ጋር በነበረው የሥራ ግንኙነት ምክንያት፣ ያንን ታላቅ የህዝብ መሪ በጥልቀት ያውቁ ከነበሩ ጥቂት ሰዎች መሀል አንዱ ሓደራ ነበር። ሓደራና ተስፋዬ በሥራቸው ጠባይ ምክንያት ብዙ ጊዜ አብረው ያሳለፉ ሲሆን፣ ሓደራ የተስፋዬ የግል ጸሀፊው፣ ማስታወሻ ያዡ፣ አማካሪው ነበር ማለት ማጋነን አይሆንም። ሓደራ፣ ተስፋዬ ሲደሰት፣ ሲበሳጭ፣ በጥልቀት ሲያስብ፣ ሲጫወት እንደ ማንኛውም ሰው ሲዝናና በቅርብ ሆኖ አይቶታል። የዚያ የታላቅ መሪ ታሪክ ይጻፍ፣ ፊልሙ ይቀረጽ ቢባል ለማስረጃነት ይቀረቡ ከነበሩት ሰዎች መሀል አንዱና ዋነኛው ሓደራ ነበር። ዛሬ የሓደራን ድንገተኛ ህልፈት በቁጭት የምናስታውሰው በሱና በቤተሰቡ እንዲሁም ሀገር ወዳድ በሆኑ የኢትዮጵያ ወገኖች ላይ በደረሰው ሀዘን ብቻ አይደለም። ዛሬ የሓደራን ድንገተኛ ህልፈት በቁጭት የምናስታውሰው ወንድማችን ተለየን ብለን ብቻ አይደለም። ዛሬ የምናዝነው፣ ሀዘናችን እጥፍ ድርብ የሆነው፣ ሓደራ ብቻውን ሳይሆን ታሪካችንንም ይዞብን ሄደ ብለን ስለምንል ነው። ሓደራ የታሪካችን መዝገበ ቃላታችን ነበርና ስለተስፋዬ ደበሣይ፣ ስለዘሩ ክህሸን፣ ስለቀይ ሽብሩ የመጨረሻ ወቅቶች የታሪክ ማስታወሻችንን ይዞብን ስለሄደም ጭምር ነው።

ልቤተሰቡ መጽናናትን፣ እመኛለሁ።

# የሃደራ ስንብት

በተኮላ መኮንን

ምን ባህል ነው የማይቀየር ጎበዝን ጎበዝ ማለት ፈርተን፣
በሕይወት እያለ ሳንናገር ሲሞት ክብሩን አወድሰን?
ምን እንባላለን እባካችሁ? በእጅ ያለወርቅ አጣጥለን?
የሚሮጠውን ሳናስተውል የተኛውን ተመልክተን።

ንግርት አይደል የቆየ አባዜ እኔንም ዛሬ ጀመረኝ፡
ያጫወተኝን የማውቀውን በቀብሩ ቀን ሊያስለፈልፈኝ።

በልጅነት የአፍላ ግፊት በትግል ገመድ ተቋጥሮ፡
ለመብት ለፍትህ ሊታገል ቆርጦ
ሕብረተሰብ ሃገር ብሎ ቤተሰቡን አሸቀንጥሮ።
በከተማው ግብ ግብ በሳት መሃል ተሹለክልኮ፣
ደህና አውለኝ በቀረበት የጓዱን ጽናት አምልኮ።
ከቀበና እስከ መቀሌ፣
ከጎንደር እስከ ሰላሌ፣
ከሲዳሞ እስከ ሐረር፣
ከባሌ እስከ ሱማሌ።

አዲስ መስመር ሲዘረጋ የተበጠሰ ሲቀጥል፣

የተጋለጠውን ሲያሸሽ በአውቶቡስ አናት ሲያንጠለጥል፣
መውጭያ ቀዳዳ ሲያሰናዳ የውሸት መታወቂያ ሲያድል።
የነበረው ብልሃተኛ ዛሬ ከደጅ ወደቀ፣
ማምለጫም አላዘጋጀ ዘዴው ጥበቡ አለቀ።
ለካ እሱ ለራሱ አያውቅም ለሌላው መቆም ለምዶ፣
በቀይ ሽብር ያልጠፋ ነፍስ ሳር ላይ ወደቀ ተሰዶ።

ሕሩይ ልበልህ ገብራይ፣
ሐደራ ልበልህ ወይስ ታጋይ?
ጌብ ልበልህ አስተማሪ?
ጓደኛ ልበልህ መካሪ?

እኮ የትኛው ይሻላል ተናገር ዝምታው ይቅር?
ደረትህን በእጆችህ ይዘህ አንገትህን አታቀርቅር።

ታጋይ አልልህ ትተሃል፡
ጓደኛም አልልህ ከድተሃል፣
ጀግና እንዳልልማ ተረተሃል።
አደራ አደራ መስጠት ይወዳል አመለም ልማደኛ፣
ቤተሰቡን ሰብስበሽ ያዢ አይመለስም ዳግመኛ።

እኔ ግን አላለቅስም ለተሰናበተኝ ጓደኛ፣
የመጨረሻይቱን ቀን፡ ላጋራኝ ወንድም ለጨከነ መንገደኛ።
ኧረ እኔ አላለቅስም ማልቀስ ታሪክ ለሌለው፣
ሃደራ ያልተወራለት ታጋይ ያልተጻፈ ገድል አለው።
ኧረ እኔ አላለቅስም በጭራሽ የማዝነው ያሰበውን ሳይጨርስ፣
ምስክርነቱን ሳይከትብ ላላወቁ ሳያዳርስ
ለልጆቹ ሳይናገር ያለፈ ታሪኩን ሳያቃምስ
እንደ  ተራ ቀላል ሰው የመቃብር አፈር ሲልስ።

በል በቃ ደህና ሁን ወንድማችን
ታጋይ አንልህ ትተሃል
ጓደኛም አንልህ ከድተሃል
ጀግና እዳንልማ ተረተሃል፣
ቆራጥ ብለን እንዳንጠራህ ሽንፈትን ተቀብለሃል

ጎበዝ ይወድቃል እንዴ ውጥን ጅምሩን ሳይጨርስ፣
ላይበራሪውን ሳይገነባ ማገር ጣራውን ሳያለብስ?
ይረታል እንዴ የትግል ሰው የጡረታ ቤት ሳያስቀልስ?

ምን አዲስ መልእክት ተገኘ ለነዘርኡ የሚነገር?
በጠዋት የሚያስገሰግስ የሚያስለቅቅ መኖሪያ ሸልተር?

እኮ ምንድነው እሱ እያወቅህ ያልነገርከን?
ተጠንቀቁ ሳትለን ሳንዘጋጅ የከዳህን፡
በቃሉ ይቆማል ስንል አፈ ዋሾ ያደረግሽን?

በል ከመሰለህ ደህና ሁን
ታጋይ እንዳንልህማ ትተሃል?
ጓደኛ ብለን እንዳንጠራህ ከድተሃል
ጀግና እንዳንልህ ተረተሃል
ቆራጥ ብለን እንዳንጠራህ ሽንፈትን ተቀብለሃል?
አበቃ ከእንግዲህ የምድር ቤቱ እንደ ሕልምህ ሰማይ አርገሃል።

# ሞት አጣፍጣለሁ

ፈዝዤ ... ናውዤ
ዓይኔ ከደን ሲል
ሸለብ ሲያደርገኝ
ጋደም ስል ገና፤

ጭር ባለው ውድቀት ...
በጥቅጥቅ ጨለማው
በእኩለ ሌሊቱ ...
በህልሜ አየሁህና ...

አገኘሁት ብዩ
ሕሩይ ጓዴ ብዩ ... አብሬህ እንዳልኖርኩ፤
ቀን በገፋን ቁጥር፣
ስምህ ሲበረክት፣ ስምህን እያሳከርኩ፤

ሐደራ ነው ... ፍርፍር ...
"ለቃሊጥ" ነህ ... ብፅአይ ...
ገብረፃድቅ ... ገብሬህ
"ዳዲ ... ጌብ/ጋቢ" እንጎቻህ ...

የቁልምጫው ብዛት፣ የስም ጋሻ-ጅግሬህ ...
አፌ የገባውን ... አንዱን ለጥፌብህ፣
ወይ እንድትል ብቻ ... ያፌን ወርውሬብህ ...

መቼም አያስችለኝ ...
ሚስጥሬን ዘክዝኬ አጫውትህና ...
የነገር ዳውላ አሸክምህና ...

አንተ የሁሉ አቴቴ፡ የወተት ፏፏቴ!
በትንሹ ስቀህ፣ በትልቁ ስቀህ፤

ወይ ያልኩህን ሆነህ፣ ወይም ያላልኩህን፣
ዕንግዳ ስታግድ ... አልፎ ሂያጅ ስትከውን ...

አንት ጅማተ-ጥኑ፣ አንተ ባለ ደንደስ
ጥላው አይረገጥ ... ዱካው አይዳሰስ
አንተ የሰው - ጋራ-አገር ...
የደረስጌ ዋልያ፣
አንት የመጫት አምሮት ...
የአቃቢት አውልያ፤

አረህ - ለአረህ ስትሮጥ፣ አረህ - ለአረህ ስትድህ፤
ይኸው ደስ ይበልህ ...
ልቡናህ ከረካ፣ አንተ እንዳፈተተህ፤
ጓዴ ወጉ ደርሶኝ ... የፈለግከውን ሆንኩ።

እረፍትህን ወስደህ፣ እርፍቴን ነሣኸኝ፣
እንቅልፍን ልትለጥጥ ... ከእንቅልፌ አጣላኸኝ፤
የሌለህን አመል ...
ይህን መሰል ክፋት ...
ከየት አመጣኸው?
ማነው እንካ ያለህ፣ ለምንስ ወሰድከው?
አንተ የጃልየው!
የገንፎ ገበታው ... አንተ የሰሜኑ፣ አንተ የደቡቡ፣
አንተ የምሥራቁ፣ አንተ የምዕራቡ፤
አንተ የዳሩ አገር፣ የመሃል አገሩ፣ አንተ የሁሉ አድባር፣
... አንተ የሁሉ ልጅ ....
እንቅልፌን ነጠቅኸኝ

ጨለማን ነፈግሽኝ ...
አትመጣብኝ እንደሁ ... በቀን ልንገላጀጅ::

እንዲህ በስተርጅና ... አዲስ አመል ማብቀል፣
አያድርስ ይባላል::
እኔ አንጀተ ብርቱው ... ዝምታህን ቻልኩት፣
ትናንትና ማታ ... በድንህን ሳምኩት::

የአካላቴ ሙቀት፣ ...
ያንተን ቅዝቃዜ መሸከም ተስኖት ...
ክፉኛ ነዘረኝ፤
ከአናት እስከ እግሬ ጥፍር፣
ያንተ ውርጭ አይሎ ...
ያንተ ቍር ወረረኝ::

መቼ በድፍረቴ በዚህ ብቻ ረካሁ ...
በዚህ ብቻ አበቃሁ?
ይኸውልህ ዛሬ ... የጭካኔዬን ልክ ...
ሬሳህን አዝዬ ... ፈረንጅ አገር ጣልኩት፤
አንጠልጥዬ ይዤ ...
... አሜሪካን አገር፣ ዳላስ ላይ ቀበርኩት ...
ወገኛ አይደለሁም?
... እኔም ወግ ደረሰኝ ...
ያልሆንኩት ምን አለ? ... እንደፈረደብኝ፤
ጓዴ በስተርጅና ...
ሞት አጣፍጣለሁ፣ ሙሾ ደርዳሪ ነኝ::

ጥር ፳፣ ፲፱፻፺ ዓ ም
ዳላስ፣ ቴክሳስ
ለገብረፃድቅ ሐደራ (ሕሩይ)
ከእሳቱ (ከበደ)

## መካሪያችን ሄደ

ከሥራ ባልደረቦቹ

ቋንቋ ልናመጣ ላንተ ግጥም ልንጽፍ፣
መስሎን እንደዋዛ እንዳንተ የምንጽፍ።
ብእሩም ነጠፈ ያለቦታው ገብቶ፣
ጋሼ አደራን መሳይ አርቃቂ ሰው አጥቶ።
ማነው አሁን ለኛ ተከራካሪያችን?
ከካምፓኒያችን ጋር ነገር ፈጃችን?
መስመር መስመር አስያዥ ብልህ ፊት መሪያችን?
አፍቃሪ አክባሪ ውድ መካሪያችን፡
ጥቃት የማታስገባ የልብ ወንድማችን።
ቅዳሜ ጠዋት ላይ ስልክ ደዋውለህ፣
የምትወዳቸውን ጓደኞች ጠርተህ፣
የድሮ ትዝታ ስታወጋ ውለህ ፣
የድሮ ጨዋት ስትጫወት ውለህ ፣
የመጨረሻ ሳቅ ደስ ብሎህ ስቀህ፣
ከባልንጀሮችህ ካንድ ገበታ በልተህ፣

ሕሊናን የሚገርም ክንውን አድርገህ።
አላወቁም ነበር ስንብት መሆኑን፣
የፍቅርህ መግለጫ የቅጽበት ክንውን፣
አስበህ ይመስላል ያደረከው ሁሉን፣
ለዛ ነው ሃደራ ማመን ያስቸገረን፣
ለዛነው ስንሰማ ድራማ የሆነብን።
እሁድ በጠዋቱ በጓሮ በር ወጥተህ፣
ቤተሰብ ለማርካት ያንተ እረፍት አጥተህ፣
እነደ ሁል ግዜ መስሎህ የሥራ ቀን፣
እኛም ስንጠብቅህ ሃደራ ቀረ እያልን፣
ስልክ ተመታና ማረፍክን ተረዳን።
ማወቅ ስላቃተን የሆንከውን ነገር፣
እስቲ እንጠይቅህ ትይንቱ ምን ነበር?
ከወጣህ ከቤተህ የሆነውን ነገር፣
ሳሩ ላይ ተንጋለህ ጣሩስ እንዴት ነበር?
ለጆር እማይሰማ ቢነገር ቢነገር።
ምን ሆነ እንበል ለዘመድ አዝማዱ?
የማታው ሳቅ ጠፍቶ እሁድ በጠዋቱ።
ሰቀቀን የሆነን የረበሸን ያ ነው፣
ወድቀህ ከሜዳ ላይ ዘመድ እንደሌለው።
የሚረዳህ አጥተህ ግራ ቀኝ ስትማትር፣
አልተገኘምና ለመልካሙ ሥራህ የሚመልስ ብድር።
ቀሳውስት እንዳሉት መጽሐፍም እንደሚል፣
አንድ ቀን ባምላክ ፊት ሰው ሁሉ ይቆማል፣
በምድር እያለን ልናስብ ይገባል፣
ከማርያም ልጅ ታርቀን ብንኖር ይበጃል።
የሰው ልጅ ሕይወት እንፋሎ ት ከሆነ፣
እንደ ጋሼ አደራ ለደቂቃ ታይቶ የሚበን ከሆነ፣
የተወሰኑለት ቀኖቹ ሳይመጡ፣
ሰው ሁሉ ይጠንቀቅ ይንጻ ከሐጥያቱ።